| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | *ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ከታሪክ ፡ አንድ ፡ ዐምድ ። "* |
| ርእስ ፤ | *"የአኵስም ፡ ሐውልትንና ፡ ቅርሳቅርሶችን ፡ የማስመለስ ፡ ውሳኔ ። "* |
| ደራሲ ፤ | የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ። |
| ዕለት ፤ | ዐዲስ ፡ አበባ ፥ ግንቦት ፡ 1960 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። (ቀደም ፡ ሲል ፡ በስሕተት ፡ "ፍጹም" ፡ ብለን ፡ ያወጣነው ፡ የጽሑፉን ፡ ረቂቅ ፡ ነበርና ፥ ይቅርታን ፡ እንጠይቃለን ። ) |
| መጽሔት ፤ | *"ሥልጡሕዝብና"* ፡ መዜንው ፥ ቀ፦.2011-003 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | በቅርቡ ፥ የኢ..ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ አገዛዝ ፡ ስለአኵስም ፡ አውራጃ ፡ ቅርሳቅርስ ፡ ጥበቃና ፡ ክብካቤ ፡ ከኢ.ጣልያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የተዋዋለውን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የመወዳጃ ፡ ውል ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ማስታወሻ ። የካቲት ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1943 ፡ ዓ.ም. ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትና ፡ የኢ.ጣሊ.ያ ፡ ሬፑብሊ.ክ ፡ መንግሥት ፡ በተፈራረሙት ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፥ የቀድሞ ፡ የፋሺ.ስት ፡ ኢ.ጣሊ.ያ ፡ መንግሥት ፡ የዘረፋቸውን ፡ ቅርሳቅርስ ፡ የዛሬው ፡ የኢ.ጣሊ.ያ ፡ መንግሥት ፡ ለኢ.ትዮጵያ ፡ ሳይመልስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይህን ፡ መሰል ፡ ስምምነት ፡ መፈራረም ፥ የግንቦት ፡ 1960 ፡ ዓ.ም. ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ያጸደቀውን ፡ ውሳኔ ፡ መጣስ ፡ ይኾናልና ፥ ድርጊቱ ፡ አድራጊዎቹን ፡ በሕግ ፡ ያስጠይቃል ። |

# ከታሪክ ፡ አንድ ፡ ዐምድ ።

History Column | colonne d'histoire | خانة التاريخ

## የአኵስም ፡ ሐውልትንና ፡ ቅርሳቅርሶችን ፡ የማስመለስ ፡ ውሳኔ ።

የኢ.ትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፥
ዐዲስ ፡ አበባ ፥ ግንቦት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1960 ፡ ዓ.ም. ።

---

[የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ተዘርፈው ፡ የተወሰዱት ፡ የአኵስም ፡ ሐውልትና ፡ ቅርሳቅርሶች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲመለሱ ፡ ማስገደጃ ፡ ውሳኔውን ፡ ልክ ፡ የዛሬ ፡ 51 ፡ ዓመት ፥ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሰነድ ፥ ሕግ ፡ አድርጎ ፡ አጽድቆታል ። ሥርዐት ፡ በሥርዐት ፡ እንጂ ፡ በውንብድና ፡ አይለወጥ ፣ ወይ ፡ አይሻር ፣ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አይሻሻልም ፤ በሕግነቱ ፡ ሳይለወጥ ፣ ሳይሻር ፣ ሳይሻሻል ፡ እንደጸና ፡ አኹንም ፡ ይገኛል ።

የውሳኔው ፡ የመጨረሻ ፡ ቃል ፦

*የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፥ ኢጣሊያ ፡ በውል ፡ ረገድ ፡ የሚገባትና ፡ የምታከብረውም ፡ ቋንቋ ፡ ጭንቅ ፡ ወይም ፡ የጥቅም ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ አምኖና ፡ የአባሎቹን ፡ አስተያየት ፡ ኹሉ ፡ በዚሁ ፡ እውነትና ፡ በሐውልቱ ፡ መመለስ ፡ ብልጫ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አስተባብሮ ፥*

*ሀ ፤ በዜጋ ፡ መሸጋገር ፡ ረገድ ፥ በመጪዎቹ ፡ ላይ ፡ በር ፡ እስከ ፡ መዝጋት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ነዋሪዎቹንም ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ ፡ ማስወጣት ፥ በጥሬት ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የንግድ ፡ መለዋወጥን ፡ እስከ ፡ ማቆምና ፥ መደምደሚያውን ፥ በዲፕሎማሲ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ግንኙነትን ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ ፡ ማቋረጥ ፡ ድረስ ፡ ተረማማጅ ፡ በሚኾን ፡ የጭቈና ፡ ዘዴ ፡ በግልጽና ፡ በማይቋረጥ ፡ አደራረግ ፡ በመጠቀም ፥ የአኵስም ፡ ሐውልትና ፡ ከርሱም ፡ ጋር ፡ የሚጠቀሱት ፡ ታሪካውያን ፡ መታሰቢያዎች ፡ በስድስት ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ ወደየነበሩበት ፡ ስፍራ ፡ እንዲመለሱ ፡ እንዲያደርግ ፡ ያስፈልጋል ፡ ሲል ፡ ወስኖ ፤*

***ለ ፤ ይህ ፡ ሐውልትና ፡ የሚጠቀሱት ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ ኹሉ ፡ እስከተመለሱና ፥ ከነርሱም ፡ መመለስ ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ የሚመለሰው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክብር ፡ ተሠይሞ ፥ የኹለቱ ፡ ሀገሮች ፡ ወዳጅነት ፡ በንጹሕ ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ ከመመሥረቱ ፡ በፊት ፥ የዳበረ ፡ ፍቅር ፡ መገለጫ ፡ የኾነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጕብኝት ፡ ክብር ፡ ቀድሞ ፡ እንዳይሰጣት ፥ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ አገር ፡ መኼድ ፡ እስከዚህ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ እንዲዘገይ ፡ ያሳስባል ። "***

ይላል ።

ውሳኔው ፡ በወቅቱ ፡ በምክር ፡ ቤቱ ፡ በሙሉ ፡ ድምፅ ፡ ጸድቆ ፡ ቢያልፍም ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ክልክሉን ፡ ተሻምደው ፥ ኢጣሊያን ፡ በይፋ ፡ ጐበኙ ። ጕብኝቱ ፡ የታቀደው ፡ ለመስከረም ፡ መጨረሻ ፡ 1963 ፡ ዓ.ም. ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፥ ከመስከረም ፡ 27 ፡ እስከ ፡ መስከረም ፡ 29 ፡ 1963 ፡ ዓ.ም. ፡ በኢጣሊያ ፡ ሰሜናዊትና ፡ ጥንታዊት ፡ ከተማ ፡ በጄኖዋ ፡ አካባቢ ፡ ከባድ ፡ ዝናብ ፡ ዘንቦ ፥ 44 ፡ ሰዎች ፡ በጐርፍ ፡ አደጋ ፡ ሲሞቱ ፣ ከ2000 ፡ በላይ ፡ ነዋሪዎች ፡ ተፈናቅለው ፥ ዐያሌ ፡ ንብረትና ፡ ቅርሳቅርስ ፡ ወደሙ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ጕብኝቱ ፡ ተሻዝሞ ፥ ለጥቅምት ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1963 ፡ ዓ.ም. ፡ ተዛወረ ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ኢጣሊያ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

እንዲ ፡ ደረሱም ፥ በማግሥቱ ፡ አንድ ፥ ጦሱን ፡ ቓልዘነጋ ፡ የኢጣሊያ ፡ መዜኛው ፥ ጕብኝታቸውን ፡ "ገፊ" ፡ ሲል ፡ "*la carogna*" ፡ ብሎ ፡ መጻፏን ፡ እቦታው ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ መስክረዋል ።

ዘንድሮ ፡ ደግሞ ፡ የኢ.ሕ.ክ.ዴ.ግ. ፡ ይዘት ፡ በዶክተር ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ መሪነት ፥ ይህኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሕጋዊ ፡ ውሳኔ ፡ ከመጣስም ፡ ዐልፎ ፥ ኢጣሊያ ፥ በዘረፈቻቸውና ፡ እስካኹን ፡ ባልመለሰቻቸው ፡ ቅርሳቅርስ ፡ ላይ ፥ የቀኑትን ፡ የአኵስም ፡ ከተማን ፡ ሐውልቶችና ፡ ቅርሳቅርስ ፡ "*እንድትከባከብ*" ፡ መዋዋሉን ፡ አስታወቀን ። አኹንም ፡ ሕግ ፡ ተጣሰ ፤ ሕግን ፡ የጣሰ ፡ ኹሉ ፡ በሕግ ፡ መጠየቁ ፡ አይቀርም ። ጕዳዩ ፡ የደም ፡ ዋጋ ፡ አለበትና ፥ የኢ.ሕ.ክ.ዴ.ግ. ፡ ኀላፊዎች ፡ ከዶክተር ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ አንሥቶ ፡ ይህን ፡ ልብ ፡ ብለው ፥ በፍጥነት ፡ ከስሕተታቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ እናሳስባለን ።

የውሳኔውን ፡ ሙሉ ፡ ቃል ፡ እነሆ ። ]

---

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፥**

**ዐዲስ ፡ አበባ ፥**

**ግንቦት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1960 ፡ ዓ.ም. ።**

**ልዩ ፡ ኮሚቴው** ፤ ካስረጂው ፡ የውጭ ፡ ጕዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ ከተማ ፡ ይፍሩ ፡ የቀረቡለትን ፡ የፓሪስን ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ ግልባጭ ፥ ይህኑ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የካቲት ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1943 ፡ ዓ.ም. ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትና ፡ የኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ የተፈራረሙበትን ፡ ስምምነት ፡ ቅጂ ፥ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ታኅሣሥ ፡ 22 ፡ ቀን ፡ 1943 ፡ ዓ.ም. ፡ ያናገሩትንና ፡ ኢጣሊያ ፡ የተቀበለችውን ፡ የኅብረት ፡ መግለጫ ፥ በተጨማሪም ፡ ክቡር ፡ የውጭ ፡ ጕዳይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ያደረጉትን ፡ የቃል ፡ ማብራሪያ ፡ አስተካክሎ ፡ ከመረመረና ፡ ከተገነዘበ ፡ በኋላ ፥ ስለአኵስም ፡ ሐውልት ፡ (**ክዋኒት**) ፡ እና ፡ ስለቀሩትም ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ ያለውን ፡ ጠቅላላ ፡ ኹኔታ ፡ ባጪሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ ኾኖ ፡ አግኝቶታል ።

**1 ፤ በውል ፡ ረገድ ፤**

1.1 ፤ ኹለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፥ በቃል ፡ ኪዳን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ባንድ ፡ ወገን ፥ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደሞ ፡ ጠላት ፡ መንግሥታት ፡ በኅብረታቸውና ፡ በየግላቸው ፡ የሚያከብሩትን ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ በጥር ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1939 ፡ ዓ.ም. ፡ (10 January 1947) ፡ ፓሪስ ፡ ላይ ፡ ሲፈርሙ ፥ በጠቅላላ ፡ አጠቃቀስ ፡ በአንቀጽ ፡ 33 ፡ ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ነጻና ፡ በራሷ ፡ ዐደር ፡ መንግሥትነቷን ፡ አረጋግጣ ፡ ዐውቃ ፥

1.1.ሀ ፤ በአንቀጽ ፡ 45 ፡ በጦርነቱ ፡ ዘመን ፡ በሰላምና ፡ ሰብኣዊ ፡ ፍጥረት ፡ ላይ ፡ ጥፋትን ፡ ያዘዙትንና ፡ በደልን ፡ ፈጽመው ፡ በብሔሯ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የራሷንና ፡ የሌላ ፡ አገር ፡ ዜጎችንም ፡ ጭምር ፡ ይዛ ፡ ለፍርድ ፡ ልታሳልፍና ፡ በወንጀል ፡ ግብራቸው ፡ ላይ ፡ ኹሉ ፡ ምስክሮችን ፡ ልታቀርብ ፤

1.1.ለ ፤ በአንቀጽ ፡ 74 ፡ ለጦር ፡ ካሳዋ ፡ 25 ፡ ሚልዮን ፡ ያሜሪካን ፡ ዶላር ፡ ወይም ፡ 62.5 ፡ ሚልዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ልትከፍልና ፥

1.1.ሐ ፤ በአንቀጽ ፡ 37 ፡ እና ፡ በአንቀጽ ፡ 75 ፡ ደግሞ ፥ በጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ በዘረፋና ፡ በሌላ ፡ በማንኛውም ፡ አኳኋን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የወሰደቻቸውን ፡ መታሰቢያዎች ፤ ንዋየ ፡ ቅድሳትንና ፡ ታሪካውያን ፡ ዕቃዎችን ፥ እንደዚሁም ፡ መዛግብትንና ፡ ሰነዶችን ፤ ወርቆችንና ፡ ሀብቶችን ፡ ኹሉ ፡ በጥሩ ፡ ኹኔታና ፡ በራሷ ፡ ኪሳራ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ብሔር ፡ አውጥታ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልታስረክብ ፡ ግዴታ ፡ ፈርማለች ፤ ከዚያም ፡ ወዲህ ፥

1.2.ሀ ፤ ይህኑ ፡ መሠረታዊ ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትና ፡ የኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ የካቲት ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1948 ፡ ዓ.ም. ፡ ባደረጉት ፡ የጠቅላላ ፡ መሳተፍ ፡ ውል ፡ ላይ ፥ ኢጣሊያ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እ"ባንኮ ፡ ዲ ፡ ሮማ" ፡ የምታኖረውን ፡ 16.3 ፡ ሚልዮን ፡ ያሜሪካ ፡ ዶላር ፡ ወይም ፡ 40.75 ፡ ሚልዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ አስተዳደር ፡ ጕዳይ ፥ ሰፋ ፡ ባለ ፡ ዝርዝር ፡ ከተግባቡ ፡ በኋላ ፥ ከኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የተመለሱትን ፡ የዕቃዎች ፡ ዝርዝር ፡ በዐባሪ ፡ አ. ፡ (ANNEX A) ፡ ላይ ፡ አስፍረው ፥ ወደፊት ፡ ተፈልገው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሚላኩትን ፡ ዝርዝር ፡ ደግሞ ፡ በዐባሪ ፡ በ. ፡ (ANNEX B) ፡ አመልክተው ፥ እነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ የሚገኙበትን ፡ ስፍራና ፡ ኹኔታ ፡ ተከታትሎ ፡ መረጃን ፡ የሚያቀርብ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ መልክተኛ ፡ ይህ ፡ ውል ፡ በጸና ፡ በ 30 ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በየበኩላቸው ፡ ሊልኩ ፡ ተስማምተው ፥ በፓሪስ ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ ላይ ፥ በአንቀጽ ፡ 37 ፣ 74 ፣ 75 ፡ እና ፡ 79 ፡ የተዘረዘሩት ፡ የኢጣሊያ ፡ ግዴታዎች ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ስምምነት ፡ በሚያረካ ፡ አኳኋን ፡ ሞልተው ፡ የተፈጸሙና ፥ በነዚህ ፡ አ. ፡ በ. ፡ ሠ. ፡ ዐባሪዎች ፡ (ANNEXES A, B, C) ፡ ባሉት ፡ ብቻ ፡ የተተኩ ፡ አድርገው ፡ ጨርሰዋል ።

የአኵስምን ፡ ሐውልት ፡ ግን ፥ ይህ ፡ ውል ፡ በጸና ፡ በስድስት ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ የኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፥ በራሱ ፡ ጥንቃቄ ፣ ኀላፊነትና ፡ ኪሳራ ፡ ነቅሎና ፡ ጠቅልሎ ፡ ናፖሊ ፡ ላይ ፥ ኢትዮጵያ ፡ ለምትመርጠው ፡ መርከብ ፡ ሊያስረክብ ፡ በዐባሪ ፡ ሠ. ፡ (ANNEX C) ፡ ግዴታ ፡ ገብቷል ።

1.2.ለ ፤ ይህ ፡ ውል ፡ የጠቅላላ ፡ ሀገሪቱን ፡ የወግና ፡ የታሪክ ፡ ዕቃዎችን ፣ መታሰቢያዎችንና ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳትን ፣ መዛግብትንና ፡ ሰነዶችን ፥ እንደዚሁም ፡ ወርቆችንና ፡ ገንዘቦችን ፡ ኹሉ ፥ የሚመለከት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ለሕዝብ ፡ ምር ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ጸድቋል ።

2 ፤ ባፈጻጸም ፡ ረገድ ፤

2.1.ሀ ፤ የኢጣሊያ ፡ ሕዝብ ፥ አብዛኛው ፥ በተለይም ፡ ማኀበራውያኑ ፡ (ሶሲያሊስቶችና ፡ ማርክሲስቶች) ፥ ንጉሣውያን ፡ የተባሉት ፡ የፖለቲካ ፡ ወገኖች ፡ በሙሉ ፥ የአኵስም ፡ ሐውልት ፥ የቀሩትም ፡ መታሰቢያዎች ፥ የመንግሥትና ፡ የግል ፡ የወግ ፡ ዕቃዎች ፣ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትና ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፥ ሌሎችም ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ ኹሉ ፥ በሙሉ ፡ ጥር ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1939 ፡ ዓ.ም. ፡ በፈረምነው ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ በገባነው ፡ ግዴታና ፥ ቀጥሎም ፥ ወደን ፡ በተቀበልነው ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ደንብ ፡ (U.N. Charter) ፡ መሠረት ፥ ለኢትዮጵያ ፡ በክብር ፡ እንዲመለሱ ፡ ያስፈልጋል ፤ ይህም ፡ መኾኑ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ተገቢ ፡ ካሳዋ ፡ ሲኾን ፥ ለኢጣሊያ ፡ ደግሞ ፡ ከጦር ፡ አንሺነት ፡ ወንጀል ፡ የሚያነጻት ፡ ክብር ፡ ከመኾኑ ፡ ጋራ ፥ በኹለቱ ፡ አገሮች ፡ ወዳጅነት ፡ መኻከል ፡ የተፈጠሩትን ፡ መሰናክሎች ፡ አስወግዶ ፥ ለፖለቲካና ፡ ለጥሪት ፡ መሳተፍ ፡ ተግባር ፡ ሰፊ ፡ ጎዳናን ፡ የሚከፍት ፡ ድርጊት ፡ ይኾናል ፡ ሲል ፡ በግልጽ ፡ ይደግፋሉ ።

2.1.ለ ፤ በመንግሥቱም ፡ በኩል ፥ የፋሺስት ፡ አገዛዝ ፡ ትዝታ ፡ ከሚሰማቸው ፡ ጥቂቶች ፡ አባሎች ፡ በቀር ፥ ሌሎች ፡ የአብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ አስተያየት ፡ ያረፈበትን ፡ እውነት ፡ በመከተል ፡ በክብር ፡ መመለሳቸውን ፡ ይደግፋሉ ፤ ስለ ፡ ኾነም ፥ በኢትዮጵያ ፡ በኩል ፡ ሕዝቡ ፡ ለሐውልቱና ፡ ለቀሩትም ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ መመለስ ፡ ጕዳይ ፡ ደንታም ፡ የለው ፡ ብለው ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ከማመናቸውም ፡ በላይ ፥ ከመንግሥቱም ፡ አባሎች ፡ መኻከል ፡ ሐውልቱ ፡ ራሱ ፡ ከሚመጣ በለውጡ ፡ ሰፊ ፡ ጥቅም ፡ የምታገኝበት ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ መቀበል ፡ ይሻላል ፥ የሚሉ ፡ መኖራቸው ፡ ለሐውልቱ ፡ መመለስ ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ የነሱ ፡ እስኪመስሉ ፡ ድረስ ፡ ያላሰቡበት ፡ ኾነዋል ።

2.2.ሀ ፤ በኢትዮጵያ ፡ በኩል ፡ የፓሪስን ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፡ ዴሞክራቲክ ፡ ኢጣሊያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የገባቻቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ለማስፈጸም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥትና ፡ የኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ የካቲት ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1948 ፡ ዓ.ም. ፡ የተፈራረሙት ፡ ስምምነት ፡ በአኵስም ፡ ሐውልትና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በሚጠቀሱት ፡ ጥንታውያን ፡ ቅርሶች ፡ ረገድ ፡ ገና ፡ ሞልቶ ፡ ያልተፈጸመ ፡ መኾኑ ፡ ተረጋግጧል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የኅብረት ፡ አስተያየቱን ፡ በይፋ ፡ የሚገልጽበት ፡ ድርጅትና ፡ ሕዋስ ፡ እስካኹን ፡ ያላበጀ ፡ በመኾኑ ፥ ስለአኵስም ፡ ሐውልትና ፡ ስለቀሩትም ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ ያለው ፡ ዐይነተኛ ፡ አስተያየት ፡ በጽሑፍ ፡ ተገልጾ ፡ ባናየውም ፥ ስለነዚሁም ፡ ታሪካውያን ፡ ረጃቶች ፡ ኹላችንም ፡ በየልቦናችን ፡ በምናኖረው ፡ የመቈርቈር ፡ ስሜት ፡ ዐይነት ፡ የሚቃጠል ፡ መኾኑ ፡ አይጠረጠርም ።

2.2.ለ ፤ የኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ስለአኵስም ፡ ሐውልት ፡ በየስምምነቱ ፡ የገባውን ፡ ግዴታ ፡ ከፍጻሜ ፡ እንዲያደርስ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ በቃልና ፡ በደብዳቤ ፡ መጠየቁ ፡ ተነግሯል ።

3 ፤ አስተያየት ።

ኮሚቴው ፡ ጕዳዩን ፡ በዝርዝር ፡ መርምሮ ፡ ይህን ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፥ ኢጣሊያኖች ፡ ዘርፈው ፡ የወሰዷቸው ፡ የአኵስም ፡ ከዋኒትና ፡ የይሁዳ ፡ አንበሳ ፡ ሐውልት ፥ እንደዚሁም ፡ እላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ውሎች ፡ የተዘረዘሩት ፡ ሌሎች ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ መመለስ ፡ ጕዳይ ፡ እንዲፋጠን ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፥

3.1 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የኅብረት ፡ አስተያየቱን ፡ ለይፋው ፡ የሚገልጽባቸውን ፡ ድርጅትና ፡ ሕዋስ ፡ ስላላበጀ ፥ የሕዝብነቱ ፡ ወኪል ፡ የኾነው ፡ የሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በጕዳዩ ፡ ላይ ፡ የሚያደርገው ፡ ንግግር ፡ በጋዜጣ ፡ እንዲወጣ ፣ በራዲዮ ፡ እንዲነገርና ፣ በቴሌቪዥን ፡ እንዲታይ ፡ ማድረግ ።

3.2 ፤ የመንግሥቱ ፡ አባሎች ፡ አስተያየት ፡ ሀገሪቱ ፡ ባገኘችው ፡ የሰላም ፡ ውልና ፥ ቀጥሎም ፡ የግርማዊነታቸው ፡ መንግሥት ፡ ከኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ባደረገው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ሐውልቱና ፡ ስለ ፡ ታሪካውያን ፡ ዕቃዎች ፡ ፈጥኖ ፡ መመለስ ፡ ጕዳይ ፡ ብቻ ፡ እንዲተባበር ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ስለታየው ፥ የሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ የወል ፡ ጉባኤ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንዲቀርብ ፡ ሲል ፡ ያዘዘውን ፡ የውሳኔ ፡ ረቂቅ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነድፎ ፡ አቅርቧል ።

## ውሳኔ ።

በሰላማዊነቷ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ በኾነችዋ ፡ በመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ አባል ፡ በመኾን ፡ ጓደኛዋ ፡ በነበረችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፥ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ የዋለችውን ፡ የግፍ ፡ ወረራና ፡ ያስከተለው ፡ ጭካኔ ፡ በሀገሪቱ ፡ ላይ ፡ የጣለውን ፡ መከራ ፡ ኢጣሊያ ፥ ኹለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ፍትሕን ፡ እንድታከብር ፡ ባስገደዳት ፡ ጊዜ ፥ ከግብረ ፡ ገብነት ፡ ውጭ ፡ በሕገ ፡ ወጥነት ፡ የተፈጸመ ፡ የአረመኔነት ፡ ወንጀል ፡ ነው ፡ ስትል ፡ አውግዛ ፥ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ በታኅሣሥ ፡ 22 ፡ ቀን ፡ 1934 ፡ ዓ.ም. ፡ የወደፊት ፡ ትውልዶችን ፡ ከጦርነት ፡ መከራዎች ፡ ለማዳን ፥ የሰውን ፡ ልጅ ፡ መሠረታውያን ፡ መብቶችን ፣ ክብርንና ፡ ዋጋን ፥ እንደዚሁም ፡ የወንድንና ፡ የሴትን ፣ የታናናሽና ፡ የታላላቅ ፡ ሀገሮችንም ፡ እኩልነት ፡ አረጋግጦ ፡ ለመመሥረትና ፡ ፍትሕን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ከአህጉራውያን ፡ (international) ፡ ስምምነቶችና ፡ ከርትዕ ፡ የሚፈልቁትንና ፡ ግዴታዎች ፡ ለማስከበር ፥ እንደዚሁም ፡ በተስፋፋ ፡ የሰው ፡ ነጻነት ፡ መኻከል ፡ የሕዝብን ፡ የሥልጣኔ ፡ ርምጃ ፡ ለመደገፍ ፥ በጥር ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1939 ፡ ዓ.ም. ፡ ፓሪስ ፡ ላይ ፡ በዋለው ፡ የሰላም ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነጻነትና ፡ በራሷ ፡ ዐደር ፡ መንግሥትነቷን ፡ ዐውቃና ፡ አረጋግጣ ፡ ተቀብላ ፥

1 ፤ በጦርነቱ ፡ ዘመን ፡ በሰላምና ፡ በሰብኣዊ ፡ ፍጥረት ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ ፈጽመው ፡ የሚገኙትን ፡ የራሷንና ፡ የሌላ ፡ አገር ፡ ዜጎችን ፡ ይዛ ፡ ለፍርድ ፡ ልትሰጥና ፥ በወንጀል ፡ ግብራቸውም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምትጠይቃቸውን ፡ ምስክሮች ፡ ልታቀርብ ፤

2 ፤ ለጦር ፡ ጕዳት ፡ ካሳዋ ፡ 25 ፡ ሚልዮን ፡ ያሜሪካ ፡ ዶላር ፡ ወይም ፡ 62.5 ፡ ሚልዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ልትክስ ፤


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

3 ፤ በጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ በዘረፋና ፡ በሌላ ፡ በማንኛውም ፡ አኳኋን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የወሰደቻቸውን ፡ መታሰቢያዎች ፣ ንዋየ ፡ ቅድሳትንና ፡ ሌሎች ፡ ታሪካውያን ፡ ዕቃዎች ፣ ሰነዶችንና ፡ መዛግብትን ፣ ወረቀቶችንና ፡ ገንዘቦችን ፡ ኹሉ ፡ በጥሩ ፡ ኹኔታና ፡ በራሷ ፡ ኪሳራ ፡ ከኢጣሊያ ፡ መሬት ፡ አውጥታ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልታስረክብ ፡ ወዳ ፥ ሌሎችም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ፍትሖች ፡ ልትፈጽም ፡ በታላቅ ፡ ወግ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብታ ፡ ፈርማ ፡ ነበር ።

ባፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ ግን ፥ በጦርነቱ ፡ ፍጻሜ ፡ በሕዝቧ ፡ እውነተኛ ፡ ስሜት ፡ ተገዳ ፡ ስለሰላም ፡ ዕርቅ ፡ ዴሞክራት ፡ ኾና ፡ ሰልታ ፡ የቀረበቸው ፡ ኢጣሊያ ፡ በሰላሙ ፡ ውል ፡ መከታ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በተገኘው ፡ ፋታ ፡ በባለሥልጣኖቿ ፡ የኰራት ፡ ስሜት ፡ ተለውጣ ፥ ፍጹም ፡ በኾነ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የገባቻቸውን ፡ የፍትሕ ፡ መሠረቶች ፡ ረስታ ፥ ኢትዮጵያን ፡ ስታስብ ፡ ወደማያስተኛት ፡ የጠላትነትም ፡ ስሜት ፡ ተመልሳ ፥ የጦር ፡ ወንጀለኞችን ፡ አሳልፋ ፡ ለፍርድ ፡ በመስጠት ፡ ረገድ ፡ ፈጽማ ፡ አልበገር ፡ እንዳለች ፥ ኢትዮጵያ ፡ ወደጥንት ፡ የባሕርይ ፡ ወሰኗ ፡ ለመመለስ ፡ ሰላማዊ ፡ ፖለቲካዋን ፡ በምትመራበትና ፥ ትኽክለኛና ፡ ሕገኛ ፡ አቤቱታዋን ፡ ለተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ በምታቀርብበት ፡ ጊዜ ፥ በነዚህ ፡ የሀገር ፡ ክፍሎች ፡ መኻከልና ፡ በዓለም ፡ ሸንጎ ፡ ላይ ፡ በተቻላት ፡ የገንዘብ ፣ የፖለቲካና ፡ የዲፕሎማሲ ፡ መሣሪያዎች ፡ ኹሉ ፡ አለመቈጠብ ፡ እንደተቃወመች ፡ የጦር ፡ ካሳዋን ፡ ገንዘብ ፡ ቀንሶ ፡ ለማስቀረት ፡ እንደጣረችና ፡ እንደኾነላትም ፡ ታይቷል ።

ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ በዐሥር ፡ ዓመት ፡ የሰላም ፡ ሥራ ፡ ያከናወነችው ፡ የራሷ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ውጤት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰፊ ፡ ገበያን ፡ እንድትፈጥር ፡ ባስገደዳት ፡ ጊዜ ፥ በኢትዮጵያ ፡ ያሉ ፡ ዜጎቿ ፡ ንብረትና ፡ ሥራ ፡ የውል ፡ መድን ፡ የሌላቸው ፡ መኾኑ ፡ የንግድ ፡ ፍላጎቷን ፡ እፍጻሜ ፡ እንዳይደርስ ፡ የሚቃወማት ፡ ስለ ፡ ኾነባት ፥ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በኀይል ፡ ወራ ፥ ሕዝቧንና ፡ ሰራዊቷን ፡ ኹሉ ፡ ዘርፋ ፡ ወስዳ ፥ ከወንጀል ፡ ኹሉ ፡ ለረከሰው ፡ የሕዝብን ፡ ሕይወትና ፡ ነጻነት ፣ መብትና ፡ ሀብት ፡ ለመንጠቅ ፡ ላፈሰሰችው ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ ምስክር ፡ ኾኖ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፥ ሮማ ፡ ከተማ ፡ ያቆመችውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሐውልት ፡ ማንሣትና ፥ ባለቤቱ ፡ ለኾነችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ መመለስ ፡ በፋሺስት ፡ አገዛዝ ፡ ውስጥ ፡ ሳለች ፡ ከደረሰባት ፡ ግፍ ፡ ዋዱነት ፡ የሚያነጻት ፥ ከኢትዮጵያም ፡ ጋራ ፡ ጥቅም ፡ በሚኖረው ፡ ወዳጅነት ፡ የሚያስተሳስራት ፡ ምክንያት ፡ መኾኑን ፡ ስትነገር ፥ እውነትነቱን ፡ ተቀብላ ፥ የካቲት ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ባደረገው ፡ ስምምነት ፡ የአኰስምን ፡ ሐውልት ፡ በራሷ ፡ ጥንቃቄ ፣ ኀላፊነትና ፡ ገንዘብ ፡ እናፖሊ ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ አውጥታ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልታስረክብ ፡ ግዴታ ፡ ገብታ ፡ ነበር ።

ይኹን ፡ እንጂ ፥ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በፓሪስ ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ ላይ ፡ በአንቀጽ ፡ 37 ፣ 74 ፣ 75 ፣ 79 ፡ የተጣለባትን ፡ ግዴታዎች ፡ ባዲሱ ፡ ስምምነት ፡ ካስወገደችና ፥ የዜጎቿን ፡ ንብረትና ፡ ሥራ ፡ በሕግ ፡ ካስጠበቀች ፡ በኋላ ፡ ዘንታ ፡ ከመቀመጧ ፡ በቀር ፡ ከቶ ፡ ግዴታዋን ፡ ለመፈጸም ፡ አልሞከረችም ።

በዳይ ፡ ሕዝብ ፡ በሰላም ፡ ውል ፡ ከሚፈጽማቸው ፡ ግዴታዎች ፡ በላይ ፡ ጥፋቱን ፡ ዐውቆ ፡ ከልብ ፡ በመጸጸት ፥ ተበዳይን ፡ ይቅርታ ፡ ካልጠየቀና ፡ ጠቡን ፡ የሚያስታውሱትን ፡ ነገሮች ፡ ኹሉ ፡ እንዲፋቁ ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፥ የአጥቂነት ፡ መንፈሱ ፡ ከርሱ ፥ የመበቀል ፡ ፍላጎቱ ፡ ደግሞ ፡ ከተበዳዩ ፡ ልቦና ፡ ሊወገድና ፥ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ የኾነውን ፡ የወደፊቱን ፡ ወንድማማችነትን ፡ ኑሮ ፡ የሚያስገኘው ፡ ኹኔታ ፡ ሊፈጠር ፡ አለመቻሉን ፡ ኢጣሊያ ፡ አልተገነዘበችም ።

በኢትዮጵያ ፡ በኩል ፥ በቀደሙት ፡ ውሎች ፡ መንፈስ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ከባሕርይ ፡ ከሚገኘውም ፡ ደግነት ፡ ጭምር ፡ በማንኛውም ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ወዳጅነትና ፡ መግባባት ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ያልጐደለው ፡ መተባበር ፡ ሲደረግላት ፥ ኢጣሊያ ፡ በርሷ ፡ በኩል ፡ ያው ፡ የጠላትነት ፡ ስሜቷ ፡ እያሸነፋት ፥ በገባችው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ገንዘቧ ፡ ያልኾነውን ፡ ጥንታዊ ፡ ሐውልት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በማስረከብ ፡ እንኳ ፡ ለተደረገላት ፡ ሰፊ ፡ ውለታ ፡ አቻው ፡ ሊኾን ፡ የሚቃጣ ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ አልፈቀደችም ።

ለኢትዮጵያ ፥ የነገሥታቷ ፡ ገናንነት ፥ የጠቢባኗ ፡ ዕውቀት ፥ የሕዝቧ ፡ አንድነትና ፡ ጠቅላላው ፡ የሀገሪቱ ፡ ሕያውነት ፡ ግዙፍ ፡ ምሳሌ ፡ ኾኖ ፥ አኵስም ፡ ላይ ፡ የኖረውን ፡ ሐውልት ፡ ሮማ ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ የፋሺስቶች ፡ ግፈኝነት ፡ መታሰቢያ ፡ ኾኖ ፡ እንዲቈይ ፡ ወደደች ። የኢትዮጵያ ፡ ውርደት ፡ የርሷ ፡ ጌጥ ፡ እንዲኾን ፡ ፈቀደች ። ይህም ፡ ኹኔታ ፡ ከውርደት ፡ ኹሉ ፡ የከፋው ፡ በራሷ ፡ ድርጊት ፡ የሚገለጽባት ፡ ነውር ፡ መኾኑን ፡ ልታውቅ ፡ አልፈቀደችም ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፥ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ደሙን ፡ አፍስሶ ፣ ዐጥንቱን ፡ ከስክሶ ፥ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መሪነት ፡ ጠላቱን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፥ ነጻነቱን ፡ ዐድሶ ፥ የተወሰደ ፡ ሀገሩን ፡ አስመልሶ ፥ በክብር ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ እንደገና ፡ ከተቀመጠ ፡ ወዲያ ፥ ድል ፡ አድራጊ ፡ ኾኖ ፡ ድል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ኹሉ ፡ ታሪኩና ፡ ክብሩ ፡ የኾነውን ፡ ሐውልቱን ፡ ተቀምቶ ፡ መኖር ፡ ፍጹም ፡ ውርደቱ ፡ መኾኑን ፡ ስለሚያውቅ ፥ አይቀበለውም ።

ስለዚህም ፥ የኢትዮጵያ ፡ የሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በግንቦት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1960 ፡ ዓ.ም. ፡ ባዋለው ፡ የኹለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ የጋራ ፡ ጉባኤው ፥ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ኹኔታ ፡ በሰፊው ፡ አጥንቶና ፡ አመዛዝኖ ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ ኢጣሊያ ፡ ካልተጨነቀች ፥ ወይም ፡ የጥቅም ፡ ግዴታ ፡ ካልኾነባት ፡ በቀር ፥ የገባቻቸውን ፡ ውሎች ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ደንብ ፡ ጐልቶ ፡ በተገለጸው ፡ አህጉራውያን ፡ ስምምነቶችንና ፡ ብሔራዊ ፡ ርትዕን ፡ በማክበር ፡ ግዴታ ፡ መሠረት ፥ ወይም ፡ በግብረ ፡ ገብነት ፡ መንገድ ፡ የምትፈጽም ፡ እንደማትኾን ፡ ሲረዳ ፥ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፥ ኵሩውና ፡ ታሪኩን ፡ አክባሪው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ በአኵስም ፡ ሐውልት ፡ ስንኳን ፡ በመቅረቱ ፡ በመዘግየቱ ፡ እንኳ ፡ የማይስማማ ፡ መኾኑን ፡ በሚገባ ፡ ስላመነ ፤

*የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፥ ኢጣሊያ ፡ በውል ፡ ረገድ ፡ የሚገባትና ፡ የምታከብረውም ፡ ቋንቋ ፡ ጭንቅ ፡ ወይም ፡ የጥቅም ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ አምኖና ፡ የአባሎቹን ፡ አስተያየት ፡ ኹሉ ፡ በዚሁ ፡ እውነትና ፡ በሐውልቱ ፡ መመለስ ፡ ብልጫ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አስተባብሮ ፥*

*ሀ ፤ በዜጋ ፡ መሸጋገር ፡ ረገድ ፥ በመጪዎች ፡ ላይ ፡ በር ፡ እስከ ፡ መዝጋት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ነዋሪዎቹንም ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ ፡ ማስወጣት ፥ በጥሪት ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የንግድ ፡ መለዋወጥን ፡ እስከ ፡ ማቆምና ፥ መደምደሚያውን ፥ በዲፕሎማሲ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ግንኙነትን ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ ፡ ማቋረጥ ፡ ድረስ ፡ ተረማማጅ ፡ በሚኾን ፡ የጭቈና ፡ ዘዴ ፡ በግልጽና ፡ በማይቋረጥ ፡ አደራረግ ፡ በመጠቀም ፥ የአኵስም ፡ ሐውልትና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የሚጠቀሱት ፡ ታሪካውያን ፡ መታሰቢያዎች ፡ በስድስት ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ ወደየነበሩበት ፡ ስፍራ ፡ እንዲመለሱ ፡ እንዲያደርግ ፡ ያስፈልጋል ፡ ሲል ፡ ወስኖ ፤*

*ለ ፤ ይህ ፡ ሐውልትና ፡ የሚጠቀሱት ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ ኹሉ ፡ እስከተመለሱና ፥ ከነርሱም ፡ መመለስ ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ የሚመለሰው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክብር ፡ ተሠይሞ ፥ የኹለቱ ፡ ሀገሮች ፡ ወዳጅነት ፡ በንጹሕ ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ ከመመሥረቱ ፡ በፊት ፥ የዳበረ ፡ ፍቅር ፡ መግለጫ ፡ የኾነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጕብኝት ፡ ክብር ፡ ቀድሞ ፡ እንዳይሰጣት ፥ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ አገር ፡ መኼድ ፡ እስከዚህ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ እንዲዘገይ ፡ ያሳስባል ❖*


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።